# VISION ZERØ

በተሻለ ሁኔታ ደህንነታቸው የተጠበቀ መንገዶች ለሲያትል

Ø

## ቪዥን ዜሮ (VISION ZERO ) ምንድን ነው?

ቪዥንዜሮ (VISION ZERO ) በመንገዶቻችን ላይ በትራፊክ አደጋ ምክንያት የሚደርሱ የሞት እና የከባድ አደጋ ጉዳቶችን በ2030 ለማስቆም የሚደረግ አለም አቀፋዊ እንቅስቃሴ ነው። እንቅስቃሴው ደህንነታቸው በተሻለ ሁኔታ የተጠበቀ መንገዶች ለሁሉም ሰው እንዲሆን የሚያደርግ ነው።

AMHARIC

City of Seattle

SDOT
Seattle Department of Transportation

SEATTLE POLICE

## እንዴት ይሰራል?

የሲያትል ቪዥን ዜሮ (VISION ZERO ) ዘመናዊ ጎዳናዎችን ለመቀየስ ሁሉን አቀፍ እና ዳታ ላይ የተመረኮዘ ዘዴን ይጠቀማል። በተጨማሪም ተመሳሳይ ግብ ባላቸው በሌሎች ከተማዎች ውጤታማነቱ የተረጋገጠውን ህብረተሰቡን የማስተማር እና ደንቦችን የማስከበር ስራ በተግባር ላይ ያውላል።

## ይህ ለምንድን ነው በጣም አስፈለጊ የሆነው?

ሲያትል በሀገሪቱ ካሉት ደህነነታቸው የተጠበቀ ከሚባሉት ከተሞች መካከል በተደጋጋሚ የምትታወስ ቢሆንም ባለፉት ሶስት አመታት ከ35,000 የሚበልጡ አደጋዎችን እስተናግዳለች። በየአመቱም 20 የሚያህሉ ሰዎች በመንገዶቻችን ላይ ህይወታቸው ያልፋል። ይህ ደግሞ ተቀባይነት የለውም። እያንዳንዱ ሞት እና ከባድ አደጋ ለቤተሰብ፤ ለወዳጅ እንዲሁም ለማህበረሰቡ አስደንጋጭ ነው። እንደዚህ ሊሆን ግን አይገባም።

በሲያትል ከተማ በመንገዶቻችን ላይ የሁሉም ሰው ደህንነት የተጠበቀ እንዲሆን አንፈልጋለን፤ ከ8 አመት ልጆቻችን እስከ 80 አመት አያቶቻችን ድረስ። በእግር በምንጓዝበት፣ መኪና በምናሽከረክርበት፣ ብስክሌት በምንነዳበት፣መንገድ በምንሻገርበት እንዲሁም እቃ በምናጓጉዝበት ጊዜ ሁሉ ደህንነታችን እና ምቾታችን የተጠበቀ እንዲሆን እንፈልጋለን።

## ይህ ለሲያትል መንገዶች ምን ማለት ነው?

በቪዥን ዜሮ (VISION ZERO ) አማካኝነት እነዚህን ለውጦች መመልከት ይጀምራሉ:

- መልካም የአሽከርካሪ ስነ ምግባርን የሚያበረታቱ እና ከተሽከርካሪዎች ፍጥነት እና የትራፊክፍሰት ይልቅ የመንገደኞችን ደህንነት የሚያስቅድሙ የመንገድ ዲዛይኖችን
- በመኖርያ አካባቢዎች እና በሚጨናነቁ አውራጎዳናዎች ላይ ዝቅተኛ የሆኑ የፍጥነት ገደቦችን
- ከፍተኛ አደጋ የሚከሰትባቸው መተላለፊያዎችን ኢላማ ያደረገ የደንብ ማስከበርን
- የማስተማር እና የማህበረሰብ ተሳትፎዎችን

## የሚሳተፈው ማነው?

ሁላችንም።

በእለት ተለት ጉዞእችን እያንዳንዳችን በህይወታችን ላይ ለሁልጊዜ ተፅእኖ ሊያመጡ የሚችሉ ምርጫዎችን እናደርጋለን። እውነት እንነጋገር እና ሁላችንም ያለጥንቃቄ መንገድ አቋርጠን፥የቁም ምልክትን አልፈን ወይም መንገድ ለሚያቋርጡ መንገደኞች ቅድሚያ ከልክለን እናውቅ ይሆናል።በዚህም ምክንያት አብዛኞቻችን ለጥቂት የተረፍንባቸው ሁኔታዎች ይኖሩ ይሆናል።

ስለዚህ የሞትን እና የከባድ አደጋዎችን ቁጥር ወደ ዜሮ ለማውረድ ሁልጊዜ ማስተዋል የተሞሉ ውሳኔዎች ማድረግ እና አብሮ መስራትን ይጠይቀናል።

እነዚህ ውሳኔዎች እና ባህርያት እየተባበሩ የተሻለ፣ ጠንካራ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ከተማ ያደርጉናል።

seattle.gov/visionzero
#VisionZeroSEA